## በክልል ሕጎች ላይ የተገኙ ግኝቶች እና ክልል-ተኮር ምክረ ሐሳቦች

### አዲስ አበባ

የተሻሻለው የአዲስ አበባ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ.361/2003 በከተማ አስተዳደሩ ስር ክፍለ ከተማ እና ቀበሌ (አሁን ወረዳ እየተባለ የሚጠራ) መዋቅር እንደሚኖር ይደነግጋል። በተጨማሪም ክፍለ ከተሞችና ቀበሌዎች የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን ያላቸው ምክር ቤቶች እንደሚኖራቸውም ይጠቁማል። ቻርተሩ አዲስ አበባ ስንት ክፍለ ከተሞችና ቀበሌዎች (ወረዳዎች) እንደሚኖሯት ማብራሪያ አላስቀመጠም፡፡

ሆኖም የከተማውን ሥራ አስፈጻሚ አካላትና የማዘጋጃ ቤትን ስራ ለመወሰን የወጡት የተለያዩ አዋጆች ከተማዋ አሥር ክፍለ ከተሞች እንደሚኖሯት በመግለጽ ሥማቸውን ይጠቅሳሉ። አዋጆቹ የክፍለ ከተሞች እና የሥራ አስፈፃሚ አካላት እንዴት እንደሚዋቀሩ እና ምን ዐይነት ተግባራትን እንደሚያከናውኑም ይገልፃሉ።

(የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት መልሶ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ 35/2004ን ይመልከቱ።)

በተጨማሪም በቅርቡ የወጣው የአዲስ አበባ አስተዳደር የክፍለ ከተማዎች እና ወረዳዎች እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ የከተማው ቁ.72/2014 አስራ አንደኛውን ክፍለ ከተማ - ለሚ ኩራን አደራጅቷል። እነዚህ አዋጆች የክፍለ ከተሞችና የቀበሌ ምክር ቤቶች (በ2012 ወደ ወረዳ ደረጃ የተሸጋገሩት) እንዴት እንደሚዋቀሩ፣ የየክፍለ ከተማውና የወረዳው ምክር ቤት ምን ያህል መቀመጫ እንደሚኖረው፣ እንዲሁም ስንት የምክር ቤት አባላት ከየትኛው መዋቅር ወይም የምርጫ ክልል እንደሚመረጡ በግልፅ አያስቀምጡም። ስለሆነም የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦች ቀርበዋል።

### ምክረ ሐሳብ

- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየክፍለ ከተማውና የወረዳው ምክር ቤት ያሉትን የም/ቤት መቀመጫዎች ብዛት ወይም መቀመጫዎቹ የሚወስኑበትን ግልፅ እና ተጨባጭ መስፈርት በሕግ አውጪው አካል ሊወስን ይገባል።

- በክፍለ ከተማና በወረዳ ምርጫ እንደ ምርጫ ክልል የሚያገለግለው የትኛው ከተማው መዋቅር እንደሆነ በግልፅ መቀመጥ አለበት፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ ምርጫ ክልል ለወረዳ ወይም ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት የሚልከው የተወካዮች ብዛት መወሰን ይኖርበታል።

**ድሬዳዋ**

በድሬዳዋ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁ. 416/1996 መሠረት ድሬዳዋን ራሷን የቻለች ከተማ ናት። ከተማዋ ምክር ቤት እንደሚኖራት ይደነግጋል፡፡ ልክ እንደ አዲስ አበባ ከተማ ቻርተር ሁሉ የድሬዳዋ ከተማ ቻርተር የከተማ ምክር ቤት መቀመጫ ምን ያህል እንደሚሆን ያሰፈረው ነገር የለም፡፡ ቻርተሩ የምርጫ ክልሎች እንዴት እንደሚወከሉ እና እያንዳንዱ የምርጫ ክልል ስንት ተወካይ እንደሚልክ ያለው ነገር የለም፡፡ ቻርተሩ እነዚህን ጉዳዮችም ሊያጠራ ይገባል፡፡ የድሬዳዋ ከተማ ምክር ቤት አዋጅ ቁ.24/2000 33 የከተማ እና 9 የገጠር ቀበሌዎች እንደሚኖሩ ያስቀምጣል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ቀበሌ 300 አባላትን የሚይዝ ምክር ቤት እንደሚኖረው ይደነግጋል፡፡ የቀበሌ ምክር ቤት አባላት እንዴት እንደሚመረጡ፣ እንደ ምርጫ ክልል የሚያገለግለው የቱ እንደሆነ የምርጫ ክልሎቹ ስንት አባላት እንደሚልኩ ግን ያለው ነገር የለም፡፡

**ምክረ ሐሳብ**

• በከተማዋ የአካባቢ ምርጫ ለማድረግ የከተማዋ ቻርተር የሆነውን አዋጅ ቁጥር 416/1996 በመከለስ የድሬዳዋ ከተማ ምክር ቤት የመቀመጫ ቁጥርን ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

• የድሬዳዋ ከተማ አዋጅ ቁጥር 24/2000 ተከልሶ ለቀበሌ ምርጫ እያንዳንዱ የምርጫ ክልል ስንት ተወካይ ለቀበሌ ምክር ቤት እንደሚልክ መቀመጥ አለበት፡፡

• በአዋጁ የተቀመጠውን ለቀበሌ ምክር ቤት የ300 አባላት ብዛት በድጋሚ ሊጤን ይገባል፡፡

**ደቡብ ብ/ብ/ህ**

"በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በየደረጃው የሚገኙ የምክር ቤት አባላትን ቁጥር ለመወሰን የወጣው አዋጅ" ቁጥር 185/2013 አንቀጽ 4(7) ለሁሉም የተመረጡ የክልሉ ምክር ቤቶች የምክር ቤት አባላት ቁጥር ለይቶ ይደነግጋል። ይህ የሚያመለክተው ሕጉ ለወረዳ፣ ለቀበሌና ለከተማ ምክር ቤቶች የምክር ቤት አባላትን ቁጥር ከመወሰን ባለፈ በዞኑ ምክር ቤቶች በቀጥታ የሚመረጡ ተወካዮችን ቁጥር የሚወስን መሆኑን ነው። በዚህ ረገድ 7 እና ከ7 ያነሰ ወረዳዎች ባሉባቸው ዞኖች ከየወረዳው 10 ተወካዮች እንደሚኖሩ በአንቀፅ 4(3) ላይ ተደንግጓል። እንዲሁም ከ7 በላይ ወረዳዎች ባሉባቸው ዞኖች እያንዳንዱ ወረዳ በ8 የዞን ምክር ቤት አባላት ይወከላል።

የአዋጁ አንቀፅ 4(5)፣ 10 እና ከ10 በታች ቀበሌዎች ባሉበት ወረዳ እያንዳንዱ ቀበሌ 10 ተወካዮችን ለወረዳው ምክር ቤት እንደሚልክ እና አንድ ወረዳ ከ11 እስከ 24 ቀበሌዎች ካሉት እያንዳንዱ ቀበሌ 9 ተወካዮች እንደሚልክ ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ከ25 በላይ ቀበሌዎች ባሉባቸው ወረዳዎች እያንዳንዱ ቀበሌ በ5 የምክር ቤት አባላት መወከል አለበት። በአንደኛ ደረጃ ላይ የተመደቡ የከተማ ምክር ቤቶች ከየቀበሌው ከ10 እስከ 15 ተወካዮች ሲኖራቸው የደረጃ ሁለት እና ሶስት ከተሞች የከተማው ምክር ቤቶች ከ15 እስከ 20 እና ከ20 እስከ 30 የሚደርሱ ከየቀበሌው ተወካዮች ይኖሩታል። የቀበሌ ምክር ቤቶች 120 በቀጥታ የሚመረጡ ተወካዮች ይኖሯቸዋል። ስለሆነም የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦች ቀርበዋል።

**ምክረ ሀሳብ**

• በደ/ብ/ብ/ህ/ አዋጅ 185/2013 የእያንዳንዱ ወረዳ፣ ከተማ፣ ቀበሌ ምክር ቤት የመቀመጫ ብዛት አወሳሰን ግልጸኝነትን የተከተለ መሆኑ ስለሚበረታታ ሌሎች ክልሎችም ሊከተሉት የሚገባ ነው።

• የዞኑ ምክር ቤት የመቀመጫ ብዛት የሚወሰነው በወረዳው ብዛት ነው። የወረዳው ምክር ቤት መቀመጫም በቀበሌው ብዛት ላይ የተመሰረተ ነው። በዚህ አካሄድ ደግሞ የወረዳና ቀበሌዎችን አመሰራረት በግልፅ የአሰራር መመዘኛዎች በሚለይ ህግ ሊደገፍ ይገባል።

**ቤንሻንጉል ጉሙዝ**

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአዋጅ 171/2012 የወረዳው ምክር ቤት ከ60 እስከ 200 መቀመጫ እንደሚኖረው አስቀምጧል፡፡ አንድ ወረዳ በትክክል ምን ያህል መቀመጫ እንደሚኖረው የሚወስነው በወረዳው የሚኖረው የሕዝብ ብዛት ቁጥር ነው፡፡ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ባለባቸው ወረዳዎች አንድ የምክር ቤት አባል ከ1000 እስከ 1700 ሕዝብ ይወክላል፡፡ መካከለኛ የሕዝብ ብዛት ባለበት ወረዳ አንድ የምክር ቤት አባል ከ400 እስከ 864 ሕዝብ እንዲወክል ይጠበቃል፡፡ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ባለባቸው ወረዳ ደግሞ አንድ የምክር ቤት አባል ከ280 እስከ 399 ሕዝብ እንዲወክል ይጠበቃል፡፡

በዚሁ አዋጅ የከተማ ምክር ቤቶች ከ60 እስከ 200 መቀመጫ እንደሚኖራቸው ተደንግጓል፡፡ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ባለባቸው ከተሞች አንድ የምክር ቤት አባል ከ865 እስከ 1000 ሕዝብ ይወክላል፡፡ መካከለኛ የሕዝብ ብዛት ባለበት አንድ የምክር ቤት አባል ከ400 እስከ 864 ሲወክል፤ አንስተኛ የሕዝብ ብዛት ባለበት ደግሞ ከ250 እስከ 399 ሕዝብ እንዲወክል ይጠበቃል፡፡

የቀበሌ ምክር ቤቶች ልክ እንደ ሌሎቹ መዋቅሮች ሁሉ ከ50 እስከ 300 መቀመጫ ይኖራቸዋል፡፡ የክልሉ መንግሥት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች እና እጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩ አስቀድሞ በማንኛውም ሰአት የወረዳ ምክር ቤት መቀመጫዎችን ቁጥር የመቀየር መብቱ ይጠበቅለታል፡፡ ይህ አዋጅ በተጨማሪም የብሔራዊ ሸንጎ አባላት ምን ያህል እንደሚሆኑ ያስቀምጣል፡፡ አንድ 200 ሺሕ እና ከ200 ሺሕ ያነሰ ህዝብ ያለው ብሔር ብሔረሰብ እና ሕዝብ ብሔራዊ ሸንጎው ከ30 እስከ 70 መቀመጫ ይኖረዋል፡፡ ከ200 ሺሕ በላይ ሕዝብ ያለው ደግሞ ከ71 እስከ 100 መቀመጫ ይኖረዋል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ሸንጎ አባላት በቀጥታ በሕዝብ አይመረጡም፡፡ የብሔር ብሔረሰብ እና ሕዝብ ተወካይ የሆነ የክልል ምክር ቤት አባል መሆን ብቻውን የብሔራዊ ሸንጎ አባል ያደርጋል። ቀሪዎቹ ደግሞ በስሩ ካሉ በወረዳ እና ከተማ ምክር ቤቶች ውስጥ ይካተታሉ፡፡

**ምክረ ሐሳብ**

• የቤንሻንጉል ክልል በስሩ የሚገኙ የወረዳ፣ የከተማ እና ቀበሌ ምክር ቤቶችን ከእነ መቀመጫ ቁጥራቸው የያዘ ዝርዝር ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

**ጋምቤላ**

በጋምቤላ ክልላዊ መስተዳደር ያልተማከለ አስተዳደር ለማጠናከር የወጣው አዋጅ 210/2014 (ረቂቅ) አንቀፅ 70(1) ቀበሌዎች በወረዳ ምርጫ እንደ ምርጫ ክልል እንደሚያገለግሉ አስቀምጧል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 70 (2) ላይ እያንዳንዱ ቀበሌ የሚልከው ተወካይ የሚወሰነው በሕዝብ ብዛት እና በምርጫ ሕጉ በተቀመጠው መሠረት መሆኑን ይገልጻል፡፡ በተጨማሪም አንቀጽ 71 (3) የምርጫ ቀበሌው የሚወሰነው በምርጫ ቦርድ እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ አንቀጽ 71 (1) እያንዳንዱ ጎጥ በቀበሌ ምርጫ ወቅት እንደ ምርጫ ክልል ሆኖ ያገለግላል ይላል፡፡ እያንዳንዱ ጎጥ በምርጫው የሚልከው ተወካይ የሚወሰነው እንደ አካባቢው ስፋት እንዲሁም የሕዝብ ብዛት ታይቶ በምርጫ ቦርድ መሆኑንም ይጠቅሳል፡፡ በቀበሌ ምርጫ የቀበሌው አስተዳደር እና ምርጫ ቦርድ የጎጡን የወሰን ክልል ያስቀምጣሉ፡፡ ይህ አዋጅ አንድ ወረዳ እና የቀበሌ ምክር ቤት ሊኖራቸው የሚገባውን ከፍተኛ ቁጥር አላስቀመጠም፡፡ ከእያንዳንዱ የምርጫ ቀበሌ የሚላከውን ተወካይና መስፈርቱን በተመለከተ ተመሳሳይ ነው፡፡

አዋጁ የቀበሌ እና ወረዳዎችን ከእነ ምክር ቤት መቀመጫ ቁጥር ብዛት ጋር አልዘረዘረም፡፡ ይህ በወረዳ እና ቀበሌ ምርጫ የምርጫ ቦርድ እና የክልሉን መንግሥት ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና የሚያምታታ ነው፡፡ የክልሉ መንግሥት ቀበሌ እና ንኡስ ቀበሌዎች ወሰን እንዲያበጁ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚህ ረገድ የክልሉ መንግስት ምርጫ ቦርድን ቢያሳትፈው ይበረታታል፡፡ የጎጥ እና ቀበሌ ወሰን በማበጀት እና በማካለል ረገድ ግን የክልሉ መንግስት መሪ ሊሆን ግድ ነው፡፡

ከምርጫ ሕጉ በተጨማሪ ለወረዳ ምርጫዎች የምርጫ ክልሎች የሚቋቋሙበትን መንገድ በተመለከተ ስህተት አለው፡፡ ከዚሁ ጋር በተገናኘ የአዋጁ አንቀጽ 8(2) እነዚህ ጉዳዮችን የሚወስነው ክልል ነው ሲል፤ አንቀጽ 8(3) ደግሞ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊያወጣ እንደሚችል ቢያስቀምጥም የተዘጋጀ ሕግ የለም፡፡

**ምክረ ሐሳብ**

- ከላይ የተጠቀሰውን ስህተት ለማረም አንቀጽ 8(2)፥ አንቀፅ 70 እና 71 ሊሻሻሉ ይገባል
- የቀበሌ እና የወረዳ ምክር ቤት የመቀመጫ ቁጥር ለመወሰን ግልጽ መስፈርት ሊቀመጥ ይገባል
- የጋምቤላ ክልል በስሩ የሚገኙ የወረዳ፣ የከተማ እና ቀበሌ ምክር ቤቶችን ከእነ መቀመጫ ቁጥራቸው የያዘ ዝርዝር ሊያሳትም ይገባል፡፡

**ሶማሌ**

**የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 170(2009) እያንዳንዱ የወረዳ እና ከተማ ምክር ቤት የሚይዘውን የመቀመጫ ቁጥር ዝርዝር ጠቋሚ ነው፡፡**(የሶማሌ ክልላዊ መንግሥት፡ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የምክር ቤት መቀመጫዎችን ለመወሰን የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር (2009) **ይህ አዋጅ ቀድሞ የወረዳ ምክር ቤቶችን መቀመጫ የሚወስነውን አዋጅ ቁጥር 79(2001) ያሻሻለ ነው፡፡**(በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የምክር ቤት መቀመጫዎችን ለመወሰን የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 70 (2001) **አዋጁ በክልሉ ያሉትን 99 ወረዳዎች እና ከተሞች እንዲሁም የ71 ወረዳዎችን እና የከተማ ምክር ቤቶችን መቀመጫ ጠቋሚ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 79(2001) 48 ወረዳዎች ያሉ ሲሆን፣ የጅግጅጋ ከተማ ደግሞ ብቸኛው እውቅና የተሰጠው የከተማ አስተዳደር ነው፡፡ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በክልሉ የሚገኙ ወረዳዎች ቁጥር በእጥፍ ሲያድጉ፤ ተጨማሪ ከተሞችን እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሆኖም ለአዳዲሶቹ ወረዳዎች መፈጠር ጥቅም ላይ የዋለው መስፈርት አልተቀመጠም፡፡**

በወረዳ ምክር ቤቶች የሚኖረው መቀመጫ ከ60 እስከ 100 ነው፡፡ ይህ ከአዋጅ ቁጥር 79(2001) መጠነኛ ለውጥ አለው፡፡ በዚህ አዋጅ የወረዳ ምክር ቤቶች መቀመጫ ከ65 እስከ 117 ነው፡፡ ከወረዳዎቹ መካከል አነስተኛ መቀመጫ ያላቸው ቁቢ እና ደደር ናቸው፡፡ ከፍተኛ የመቀመጫ ቁጥር ካላቸው መካከል ደግሞ መኢሶ፣ ደጋሐቡር እና ዶሎ አዶ የሚጠቀሱ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው 100 መቀመጫ አላቸው፡፡ አዋጁ የቀበሌ ምክር ቤቶች ከ50 እስከ 70 እንደሚኖራቸው አስቀምጧል፡፡ (በቀደመው ጊዜ እያንዳንዱ ቀበሌ እንደሚይዘው የሕዝብ ብዛት ቁጥር በቀበሌ ምክር ቤት ከፍተኛው ቁጥር 100 ነው)፡፡ (የሶማሌ ክልላዊ መንግሥት፡ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የምክር ቤት መቀመጫዎችን ለመወሰን የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር170(2009)

ምክረ ሐሳብ

- በክልሉ አዋጅ ለ28ቱ ወረዳዎች እና የቀበሌ ምክር ቤቶች የሚኖረው የመቀመጫ ብዛት በግልጽ አልሠፈረም፡፡ በእነዚህ ወረዳዎች የሚኖረውን የምክር ቤት መቀመጫ ብዛት ለመወሰን ሕጉ ሊሻሻል ይገባል፡፡
- በሶማሌ ክልል የሚገኙ ወረዳዎች ቁጥር በፍጥነት እየጨመረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የእነዚህን አዳዲስ ወረዳዎች አፈጣጠር፣ አከፋፈል እና ውሕደት በተመለከተ ግልጽ መስፈርት ማስቀመጥ በህጉ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ታይቷል፡፡

**ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ**

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም ከአካባቢ ምርጫ ጋር በተገናኘ እስካሁን ድረስ ሕግ ባለማውጣቱ የአካባቢ ምክር ቤት፣ የመቀመጫ ብዛት እና የምርጫ ክልል ወሰንን በተመለከተ ህግ አውጥተው ሊያሳውቁ ይገባል። በዚህም ምክረ ሀሳብ መሰረት አግባብነት ያለባቸውን የህግ ማሻሻያዎች በምክር ቤቱ አስወስኖ ይህ ደብዳቤ በደረሳችሁ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ እንዲልክ ከአክብሮት ጋር እናሳውቃለን፡፡